ስለዴሞክራሲ ሂደትና ስለነጻ ምርጫ ያለንን ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ አማራጭ አስረድተን፣ ለዚህ አማራጭ የኢትዮጵያን ዴሞክራቶች ከጎናችን አሰልፈን እስካልታገልን ድረስ የትኛውም ጎዳና የሚያዋጣ አይሆንም:: ለብቻ ተንደርድሮ ምርጫ ውስጥ መግባት ለኢህአዴግ መንበርከክ ነው:: ህዝብን ሳይዙ እንሳተፍም ማለትም ብቻውን ትግላችንን ፈቅ እንደማያደርገው የዛሬ አምስት ዓመት የወያኔ መሪዎች ብቻቸውን ከተወዳደሩበትና እኛም ህዝቡን ሳንይዝና ሳናስከትል ብቻችንን በይኩት ካደረግነው ምርጫ ትምህርት ቀስመናል::

ባጭሩ ከወያኔዎች የማይረባ የግንቦት ግርግር በኋላ [illegible] የሚቀጥለው ትግላችን ጥራትም ሆነ ጥንካሬ የሚወሰነው በዚህ በፓሪሱ ሰነድ ዙሪያ በውስጥም በውጭም ተንቀሳቅሰን ዛሬ በምንፈጥረውና ቀጣይነቱንም ለማረጋገጥ ከዚህ እስከ ግንቦት ድረስ በጋራ በምንወስዳቸው ተጨባጭ እርምጃዎች ይሆናል::

እነዚህ እርምጃዎች ላይ ስንወያይ መነሻ አድርገን የምንወስዳቸው አንዳንድ ነጥቦች አሉ::

መጀመሪያ መነሻችንና ግልጽ የሆነው ነገር በኢትዮጵያ ነጻ ምርጫ ለማካሄድ ዛሬ ከዛሬ አምስት ዓመት በይበልጥ የተመቻቸ ሁኔታ የለም የሚለው ነው::

ሁለተኛ ዛሬ ከዛሬ አምስት ዓመት የተለየ ነገር ያለው በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ በሃገሪቱ አሉ የሚባሉት ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ድርጅቶች በዚህ በነጻ ምርጫ ጉዳይ ያላቸውን ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ያሰፈረ የጋራ የመታገያ ሰነድ አላቸው:: በዚህ ሰነድ ዙሪያም ለሚያካሂዱት የጋራ ትግል ቀንበር ኢተፖድሀን ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ ናቸው::

ይህ የጋራ ሰነድ በተለይ ለግንቦት ወር 1992 ዓ.ም. ምርጫ ተብሎ የተነደፈ ሰነድ አይደለም:: በህብረተሰባችን ዴሞክራሲን እስፍና ለነጻ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ለሚደረገው ትግል መመሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የተነደፈ ሰነድ ነው:: በመሆኑም መጭውን ምርጫ የትግላችን አልፋና ኦሜጋ አርገን አንወስደውም:: እንዲያውም ዛሬ በሃገራችን ያለው ሁኔታ የሚያመለክተው መጭው ምርጫ እንደቀደሙት ምርጫዎች ሁሉ ከተጭበረበረና ከሸፍጥ ሂደት እንደማያልፍ ነው:: በመሆኑም መወያየት የሚኖርብን አንደኛ እስከ ግንቦት ድረስ ስለምናካሂደው የጋራ እንቅስቃሴና ትግል ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በህድረ ግንቦቱ ወቅት ትግላችን በተጠናከረ ሁኔታ ስለሚቀጥልበት ዘዴም መሆን ይኖርበታል::

በዚህ የወያኔ ዝግጅት ሳቢያ በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲና ለነጻ ምርጫ የሚደረገውን ትግላችንን እንዴት እናግዘው? [illegible] የቅስቀሳችን ዋና ዋና ነጥቦች ምን መሆን ይኖርባቸዋል? በዚህ ትግል ውስጥ የውጩና የውስጡ የተለያዩና የሚተጋገዙ ተግባራት ምን ይሆናሉ? በሃገር ውስጥ በተለይ ለሚካሄደው ስራ የቅስቀሳና የማደራጀት ጥረት የፋይናንስና የማቴርያል ድጋፍ ለማቅረብ እንዴት እንችላለን? በውጭ የተጀመረው የድጋፍ ኮሚቴዎች የማቋቋም ተግባር ይበልጥ ሰፍቶና መልክ ይዞ ለቀጣዩ ትግል የሚያመረቃ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለው በምን ዘዴ ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሳን መልስ መስጠት ይኖርብናል::

ለነዚህ ሰፋፊና ወሳኝ ጥያቄዎች የተሟላ የጋራ መልስ ለመስጠት ያለን ጊዜ አጭር በመሆኑ አጨፋሪና በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ መታየት ያለባቸውን ነጥቦች እየተውን ቁም ነገሮች ላይ ብንወያይ ይህ ስብሰባችን እናም ሆነን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠብቀውን የሚያመረቃ ውጤት አስገኝቶ እንደሚፈጸም እርግጠኛ ነኝ:: አመሰግናለሁ::